የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፺፬
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፮ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 94
ADDIS ABABA-11th September, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም.
ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት ጋር የተደረገው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............................. ገጽ ፪ሺ፫፻፺፫

## CONTENTS

Proclamation No. 369/2003
OPEC Fund for International Development Debt Relief Agreement Ratification Proclamation ............... Page 2393

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፱/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለዕዳ ክፍያ የሚውል ፮ ሚሊዮን ፮፻ ሺ (ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር በብድር የሚያስገኘው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ ኦክቶበር ፳፱/፪ ሺ ፪ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጳጉሜ ፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለ ሆነ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት ጋር የተደረገው የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፱/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

*PROCLAMATION NO. 369/2003*

### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE DEBT RELIEF AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPECFUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT*

WHEREAS, a Debt Relief Agreement between The Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia, a Lone amount of USD 6,600,000 (six million six hundred thousand United States Dollars) to be used for debt serving was signed in Vienna, on the 29th day of October, 2002;

WHEREAS, basic economic international agre-ements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its Session held on the 11th day of September, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "OPEC fund for International Development Debt Relief Agreement Ratification Proclamation No. 369/2003."

ያንዱ ዋጋ
2.30
Unite Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ.
Negarit G.P.O. Box 80,001

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ ኦክቶበር ፳፱/፪ሺ ፪ በቪዬና የተፈረመው በሂፒክ ኢንሺዬተብ ላይ በመመሥረት የተደረገ የዕዳ ቅነሳ ስምምነት ነው።

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፮ ሚሊዮን ፮፻ ሺ (ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተ መለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጳጉሜ ፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Agreement" means the Enhanced Hipc Debt Initiative Relief Agreement signed in Vienna between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development on the 29th day of October 2002.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Lone amount of USD 6,600,000 (six million six hundred thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Agreement.

4. Effective Date

*The is Proclamation shall enter into force on the 11th day of September, 2003.*

*Done at Addis Ababa, this 11th day of September, 2003.*

*GIRMA WOLDEGIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት